ፊንላንድ

# የእርስዎ መብቶች እና የመቀበያ ግዴታዎች



የሚከተሉት ሁኔታዎች የሚመለከቱዎት ከሆነ፣ ይህ መረጃ የተዘጋጀው ለእርስዎ ነው፡-

- እድሜዎ ከ18 አመት በታች ከሆነ
- እዚህ ከአንድ ወይም ከሁለቱም ወላጆችዎ ጋር ደርሰዋል
- እርስዎና ቤተሰብዎ በፊንላንድ ውስጥ ለጥገኝነት (ዓለም አቀፍ ጥበቃ ተብሎም ይጠራል) ማመልከት እንደምትፈልጉ ለባለሥልጣኖች ነግረዋቸዋል።


እርስዎና ቤተሰብዎ በዚህ ሀገር ውስጥ ደኅንነታችሁ የተጠበቀ ነው።

AMHARIC

በአውሮፓ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ሁሉ እንደ ሕፃን ይቆጠራል፣ እንዲሁም **ልዩ ድጋፍ** የማግኘት መብት አላቸው።

## ማን ሊረዳዎት ይችላል?

በዚህች ሀገር በሚቆዩበት ጊዜ፣ ብዙ ባለሙያዎች እርስዎንና ቤተሰብዎን ሊረዱ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ **ትርጓሚ** በሚረዱት ቋንቋ እንዲነጋገሩ ሊረዳዎት ይችላል። የነሱ ሚና እርስዎ እና ሌሎች የተናገሩትን በትክክል መተርጎም ነው።



## እርስዎና ቤተሰብዎ ምን ያገኛሉ?

ባለሥልጣናት የጥገኝነት ማመልከቻችሁን በሚመረምሩበት ጊዜ የተለያዩ ዓይነት ድጋፍና አገልግሎቶችን ታገኛላችሁ። ይህ **መቀበያ (መስተንግዶ)** ይባላል።

እንደ ሕፃን እና እንደ ጥገኝነት ጠያቂ መብቶች አሉዎት፣ ነገር ግን ልታከብሯቸው የሚገቡ ግዴታዎችም አሉ። እነዚህ በዚህ መግለጫ ውስጥ ተብራርተዋል።

የዚህን መግለጫ ክፍሎች ካልተረዱ ወይም ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት፣ ሠራተኞቹንና ወላጆችዎን ይጠይቁ።

በሚቀጥሉት ቀናት ውስጥ ተጨማሪ መረጃ ታገኛላችሁ።

**በሁኔታችሁ ላይ ተመስርቶ፣ እርስዎና ቤተሰብዎ የሚከተሉትን ታገኛላችሁ፡-**



- የሚያድሩበት/የሚተኙበት ቤት/ቦታ



- ምግብ



- የግል ንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች



- ልብስ



- ለዕለት ተዕለት ወጪ የሚሆን ገንዘብ

## የጤና እንክብካቤ መብት

**ባለሥልጣናት የሚያስፈልግዎትን የጤና እንክብካቤ ማግኘትዎን ያረጋግጣሉ።**

ከነርስ ወይም ከሐኪም ጋር የሕክምና ምርመራ ማድረግ ሊኖርባችሁ እንደሚችል ሠራተኞቹ እርስዎንና ቤተሰብዎን ይነግሩዎታል።






## ለሠራተኞቹ ያሳውቁ፣ የሚከተለው ከሆነ፦


- ታመዋል፣ ተጎድተዋል ወይም አስቸኳይ የህክምና እርዳታ ይፈልጋሉ
- አካል ጉዳት ካለብዎ
- ጥቃት ደርሶብዎ ከሆነ
- አንድን ሰው ፈርተው ወይም ፍርሃት ተሰምትዎት ከሆነ
- እርጉዝ ከሆኑ ወይም ሊሆኑ ከቻለ
- እርስዎ ወይም ቤተሰብዎ ለሌላ ማንኛውም ምክንያት ድጋፍ የሚፈልጉ ከሆነ።

ብዙ ጊዜ ሀዘን፣ ቁጣ፣ ፍርሃት፣ ጭንቀት ከተሰማዎት ወይም ለመተኛት ከከበደዎት፣ **ከሠራተኞች ወይም ከነርስ** ጋር መነጋገር ይችላሉ።
ነርሱን፣ ሐኪሙን፣ ሥነ ልቦና ባለሙያውን እና ሠራተኞቹን ማመን ይችላሉ። በእርስዎ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር የሚናገሩት ነገር ከወላጆችዎ ሌላ ለማንም ሰው አይጋራም። ብቸኛው ልዩነት የእርስዎ ወይም የሌላ ሰው ሕይወት አደጋ ላይ ከሆነ ነው።

## የትምህርት መብት

እንደ ሕፃን የትምህርት እና የመማር መብት አለዎት። ሠራተኞቹ እንዲማሩ፣ እንዲያድጉ እና አዲስ ጓደኞችን እንዲያፈሩ የሚረዱዎትን የትምህርት እና የመዝናኛ እንቅስቃሴዎችን ይነግሩዎታል።





## የመሥራት መብት





በእድሜዎና በሁኔታዎ ላይ ተመስርቶ ከፈለጉ እንዲሠሩ ሊፈቀድልዎ ይችላል። ሠራተኞቹ ተጨማሪ መረጃ ይሰጡዎታል።

## እርስዎና ቤተሰብዎ የት ትቆያላችሁ?




ባለሥልጣናት የጥገኝነት ማመልከቻችሁን በሚመረምሩበት ጊዜ የምትቆዩበት ቦታ በሁኔታችሁ ላይ ይመሰረታል።

ሠራተኞቹ የት መቆየት እንዳለባችሁ ያሳውቋችኋል። **እርስዎ ድጋፍና አገልግሎቶችን የምታገኙት ባለሥልጣናት በወሰኑበት ቦታ ብቻ ይሆናል**

**ቤተሰቦች በፈለጉት ጊዜ መውጣትና መግባት ወደማይችሉበት ማዕከል የሚገቡት እጅግ በጣም አልፎ አልፎ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ከሆናችሁ፣ የሕግ አማካሪ እና ሠራተኞቹ ይረዱዎታል።**
የሕግ አማካሪ በዚህ ሀገር ውስጥ ያሉትን ሕጎች የሚያውቅ፣ ሁኔታችሁን ሊያጠና እና ሊረዳችሁ የሚችል ሰው ነው።



**የትም ተመድባችሁ ብትቆዩ የሚከተሉትን የማድረግ መብት አላችሁ፦**



- **ከቤተሰብዎ ጋር መቆየት**



- የቤተሰብዎ አባላት **የት እንዳሉ የማያውቁ ከሆነ እነሱን ለመፈለግ እና ለመነጋገር እርዳታ ማግኘት።**

**በደህንነት የመኖር መብት አልዎት። ማንም ሰው እንዲህ እንዲያደርግ አይፈቀድለትም፡**



እንዲዝትብዎ

እንዲሰድብ
ዎ

ጉዳት
ሊያደርስብዎት

ማንም ይሁኑ ማን – የማያውቁት ይሁን ወይም የሚያውቁት ሰው
ከወላጆችዎ ወይም ከሠራተኞቹ ጋር ማንኛውም ችግር ካለብዎ መናገር ይችላሉ።

## እርስዎና ቤተሰብዎ ምን ዓይነት የመቀበያ (የመስተንግዶ) ግዴታዎች አሉባችሁ?

እውነትን መናገርና ከባለሥልጣናት ጋር መተባበርዎ አስፈላጊ ነው፣ ታሪኮን ለመናገር አንዳንዴ የሚያስፈራና ከባድ ቢሆንም እንኳ።
ሠራተኞቹ ሁኔታዎን ካወቁ ሊረዱዎት ይችላሉ።

እርስዎና ቤተሰብዎ ሊያከብሯቸው የሚገቡ አንዳንድ ግዴታዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡-

- የምትቆዩበትን ቦታ ሕግጋት መከተል።
- ባለሥልጣኖች እንድትቆዩ ከነገሯችሁ ቦታ አለመሸሽ።
- ሠራተኞቹ የሚያስረዱዋችሁን የዚህን ሀገር ሕጎች መከተል።

## እርስዎ ወይም ቤተሰብዎ ግዴታዎቻችሁን ባትፈጽሙ ምን ይሆናል?

ይህ ከተፈጠረ፣ ለሠራተኞቹ በግልጽ በመናገር ሁኔታችሁን ማስረዳት ትችላላችሁ። ባለሥልጣናት ሁኔታውን ይገመግማሉ፤ አንዳንድ እርምጃዎችን ለመውሰድ ከወሰኑ ወላጆችዎን ያሳውቃሉ።



ለምሳሌ፣ የቤተሰብዎ አባል ከባለሥልጣናት ጋር ካልተባበረ፣ **ያ የቤተሰብ አባል አነስተኛ ድጋፍ ሊያገኝ ይችላል።**



የቤተሰብዎ አባል በጉልበተኝነት የሚንቀሳቀስ ከሆነ፣ **ያ የቤተሰብ አባል የሚያገኘውን ድጋፍ ሊያጣ ይችላል።** ፖሊስ ሊጠራ ይችላል።

አሁንም የሚያገኙት የድጋፍ ዓይነት በግል ሁኔታቸውና በፍላጎታቸው ላይ ይመሰረታል።

**እርስዎና ቤተሰብዎ አሁን የአውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገር በሆነችው  በፊንላንድ, ውስጥ ትገኛላችሁ። የአውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገራት የሚከተሉት ናቸው፡-**

- 27 የአውሮፓ ኅብረት (EU) አባል ሀገራት፡- ኦስትሪያ፣ ቤልጂየም፣ ቡልጋሪያ፣ ክሮኤሽያ፣ ሳይፕረስ፣ ቼኪያ፣ ዴንማርክ፣ ኢስቶኒያ፣ ፊንላንድ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ግሪክ፣ ሃንጋሪ፣ ጣሊያን፣ ላቲቪያ፣ ሊቱዌኒያ፣ ሉክሰምበርግ፣ ማልታ፣ ኔዘርላንድስ፣ ፖላንድ፣ ፖርቱጋል፣ የአየርላንድ ሪፐብሊክ፣ ሮማኒያ፣ ስሎቫኪያ፣ ስሎቬንያ፣ ስፔን፣ ስዊድን እና
- 4 ሌሎች ሀገራት፡- አይስላንድ፣ ሊችተንስታይን፣ ኖርዌይ እና ስዊዘርላንድ።

## ለጥገኝነት ለማመልከት እና ወደ አውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገራት ለመጓዝ የሚረዱ ደንቦች


- እርስዎና ቤተሰብዎ በፊንላንድ ውስጥ መቆየት አለባችሁ እንጂ ወደ ሌላ የአውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገር መሸሽ የለባችሁም።
- ብትሸሹ፣ በኋላ የሚብራሩ አሉታዊ ውጤቶች ያስከትልባችኋል። ለምሳሌ፣ በሌላኛው ሀገር አነስተኛ የመቀበያ ድጋፍ ታገኛላችሁ።



- ያስታውሱ፣ ባለሥልጣናት ሌላ ካልነገሯችሁ በስተቀር የጥገኝነት ማመልከቻችሁን ለመጀመሪያ ጊዜ የደረሳችሁበት የአውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገር ማስመዝገብ አለባችሁ።
- የጥገኝነት ማመልከቻችሁን የመመርመር ኃላፊነት ያለበት ከነዚህ ሀገራት አንዱ ብቻ ነው። በ
በፊንላንድ ውስጥ ያሉት ባለሥልጣናት የትኛው ሀገር ለዚህ ኃላፊነት እንዳለበት ይነግሯችኋል።

ስለነዚህ ሂደቶች በተለያዩ መግለጫዎች (ብሮሹሮች) ይማራሉ።

## እርስዎና ቤተሰብዎ ወደ ሌላ የአውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገር ብትሸሹ ምን ይሆናል?




**በፊንላንድ ውስጥ፡-**

- የጥገኝነት አሰራርዎ ሊቆም ይችላል።

**በሌላኛው የአውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገር ውስጥ፡-**

- ባለሥልጣኖቹ ወደ ለቀቃችሁት የአውሮፓ ህብረት (EU) + ሀገር ሊመልሷችሁ ሊወስኑ ይችላሉ።

ባለሥልጣኖቹ ስለ ውሳኔው ካሳወቋችሁበት ጊዜ ጀምሮ፣ ለአንዳንድ መብቶች ተደራሽነት አይኖራችሁም፣ ለምሳሌ፡-

- አንዳንድ የድጋፍ ዓይነቶችን አታገኙም፣ እና
- እንድትሠሩ አይፈቀድላችሁም።

አሁንም የምታገኙት የድጋፍ ዓይነት በሁኔታችሁና በፍላጎታችሁ ላይ ይመሰረታል።

## ባለሥልጣናት በወሰኑት ውሳኔ ካልተስማማችሁ እርስዎና ቤተሰብዎን ማን ሊረዳችሁ ይችላል?



ከሕግ አማካሪ እርዳታ መጠየቅ ትችላላችሁ።

ሠራተኞቹ መረጃና እርዳታ ሊሰጧችሁ ስለሚችሉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም ያሳውቋችኋል።




የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኤጀንሲ (UNHCR) በማንኛውም ጊዜ ማግኘት ትችላላችሁ። ዩ.ኤን.ኤች.ሲ.አር. (UNHCR) ሀገራቸውን ለቀው እንዲወጡ የተገደዱ ሰዎችን ይጠብቃል።

## የእኔ ማስታወሻዎች

# የእውቂያ ዝርዝሮች
እርስዎና ቤተሰብዎ ማንኛውም ጥያቄ ካላችሁ ወይም በሚቆዩበት ጊዜ ድጋፍ ካስፈለጋችሁ፣ በሚከተሉት ውስጥ ከሚሠሩ ሠራተኞች ጋር መነጋገር ትችላላችሁ፦

**አግባብነት ያለው ባለሥልጣን**

የእርሶ የመቀበያ ማዕከል

**ሌላ አግባብነት ያለው ባለሥልጣን**

የኢሚግሬሽን ቢሮ (Maahanmuuttovirasto)

ፖ.ሳ.ቁ. 10, FI-00086 Maahanmuuttovirasto, ኢሜይል: migri@migri.fi

**የሕግ ምክር፣ የሕግ እርዳታ እና የሕግ ውክልና**

የሕግ እርዳታ በመንግስት የሕግ እርዳታ ቢሮዎች፣ በሕግ ቢሮዎች እና በጠበቆች ይሰጣል።

ስለ የሕግ ተወካዮች ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ የሚኖሩበትን መቀበያ ማዕከል ይጠይቁ።

ድህረ ገጽ: oikeuspalveluvirasto.fi/yhteystiedot

**UNHCR (የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን)**

UNHCR የጥገኝነት ጠያቂዎችን እና ስደተኞችን መብቶችና ጥቅሞች ይጠብቃል።

ቅርብ የUNHCR ክልላዊ ቢሮ:

United Nations High Commissioner for Refugees (UNHCR)

አድራሻ: Wenner-Gren Center, Sveavägen 166, 11346 Stockholm, Sweden

ኢሜይል: swest@unhcr.org

ሌሎች የመገናኛ አድራሻዎች

የእኩልነት ኦምቡድስማን (Yhdenvertaisuusvaltuutettu),ፖ.ሳ.ቁ. 24, FI-00023 Valtioneuvosto, ኢሜይል: yvv@oikeus.fi , ድህረ ገጽ: www.syrjinta.fi

ድንገተኛ የሕክምና ችግር ካለብዎት ወይም በአደጋ ውስጥ ከሆኑ፣ በነጻ ወደ 112 የአስቸኳይ ጊዜ ስልክ ቁጥር መደወል ይችላሉ።

ይህ ብሮሸር ለመረጃ አገልግሎት ብቻ የሚውል ነው። በራሱ መብቶችን ወይም ግዴታዎችን አይፈጥርም። የአውሮፓ ኅብረት የጥገኝነት ኤጀንሲ (EUAA) የዚህን ጽሑፍ ዋና ክፍል አቅርቧል፣ እና የዚህ መግለጫ ቅጂ ማውጣትና ማሻሻያ ማድረግ የተፈቀደው ለአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ብቻ ነው። የEUAA በአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ወይም በሌላ ማንኛውም ኃላፊነት ባለው ሶስተኛ ወገን በዚህ ብሮሸር ውስጥ የተካተተው መረጃ ትክክለኛነት፣ ይዘት፣ ሙሉነት፣ ሕጋዊነት ወይም አስተማማኝነት ላይ ምንም ዓይነት ኃላፊነት ወይም ተጠያቂነትን አይቀበልም። በዚህ ብሮሸር ላይ ካለ መረጃ ሊገኝ ስለሚችል ጥቅም EUAA ሆነ ማናቸውም በEUAA ስም የሚሰራ ማናቸውም ሰው ኃላፊነት አይወስድም።

© የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ድርጅት (European Union Agency for Asylum)፣ 2025

Publications Office
of the European Union

ISBN 000-00-00-00000-0
doi:00.0000/0000000
AA-00-00-000-AM-C